**ስለአትሌቲክስ እና ከመደበኛ ከሪኩለም ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ላይ ስለሚፈጸም፣ ዛቻ፣ ማስፈራራት፣ ማሸማቀቅ፣ ማስጨነቅ፣ ጥቃት ሪፖርት የማስተላለፍ ስምምነቶችን ጨምሮ የቁጥጥርና ክትትል ጉዳዮችን ማወቅ/መረዳት**

ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የውጭ ግምገማ ውጤት ማጠቃለያ እና አስተያየቶች

## I የግምገማ ቅደምተከተል

- ከተማሪዎች፣ ከመምህራን፣ የአትሌቲክስ ዳይሬክተሮች፣ የአክቲቪቲ ስፖንሰሮች፣ አሠልጣኞች፣ የዲስትሪክት መሪዎች እና የሌሎችም ጉዳዮ የሚመለከታቸው ቃለመጠይቆች ተካሄደዋል
- በአትሌቲክስ ላይ ዛቻ፣ ማስፈራራት፣ ማሸማቀቅ፣ ማስጨነቅ፣ እና ጥቃትን በመከላከል ረገድ ከሪጅኑ ሰፋፊ የትምህርት ቤት ዲስትሪክቶች የአትሌቲክስ አስተባባሪዎችን እና አገር አቀፍ ኤክስፐርቶችን ጭምር ያካተተ የውይይት ስብሰባዎች ተደርገዋል
- አስፈላጊ የሆኑ ሠነዶች ግምገማ እና የኋላ ታሪክ ማቴሪያሎች ማጣራት ተደርጓል
- የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ክሱልስ (MCPS) በሥራ ላይ ያሉትን ፖሊሲዎች እና የእኛ ሪኮመንዴሽኖች ከአገርአቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎች ጋር እንዲጣጣሙ ተደርጓል

* እነዚህ የግምገማ ውጤቶች እና ሪኮመንዴሽኖች/አስተያየቶች የግድ ውስንነት አላቸው። ቃለመጠይቆች፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ቡድኖች፣ እና ጥናት የተደረገባቸው ጉዳዮች አጠቃላይ በዲስትሪክቱ ያሉትን እያንዳንዱን ትምህርት ቤት አይዳሥስም።

## II. አወንታዊ/መልካም ባህልን ማዳበር-ማበረታት

### የግምገማ ግኝቶች

- በአጠቃላይ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክስ ስኩልስ (MCPS) በአትሌቲክስ እና ሌሎች ከመደበኛ ትምህርት ውጪ የሚካሄዱ አክቲቪቲዎች/እንቅስቃሴዎች ዙርያ አወንታዊ/መልካም ባህልን እያዳበረ መሆኑን ገምጋሚዎቹ ተገንዝበዋል
- በዚህ ወቅት በአትሌቲክስ እና ሌሎች ከመደበኛ ትምህርት ውጪ በሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች ዙርያ በደማስከስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም እኛ በጎበኘናቸው በሌሎች ትምህርት ቤቶች ውስጥ ዛቻ፣ ማስፈራራት፣ ማሸማቀቅ፣ ማስጨነቅ፣ እና ጾታዊ-ወሲባዊ ጥቃት የሚስፋፋበት ምንም ማስረጃ አልተገኘም

ማሳሰቢያ፡- ገምጋሚዎቹ ሁሉን የሚያጠቃልል፣ ሪፖርት ያልተደረጉ ክስተት ታሪኮችን ግምገማ አላደረጉም።

- ስለጥቃት የሚያውቁ ቢሆንም ተማሪዎች ስለ ማሳፈር/ማዋረድ ግን ያላቸው ግንዛቤ ጥቂት ነው።
- ከአስተዳዳሪዎች፣ ከአትሌቲክስ ዳይረክተሮች፣ ከአሠልጣኞች፣ እና ከመደበኛ ትምህርት በተጨማሪ የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎችን ስፖንሰር የሚያደርጉት የሚናገሩበት ድምፅ ለዛ በተማሪዎች ባህርይ ላይ እጅግ አስፈላጊ ተፅእኖ ይፈጥራል።

### አስተያየቶች

- ለተማሪ አትሌቶች እና ከመደበኛ ትምህርት ሌላ ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ላይ ለሚሳተፉት ስለ ማሳፈር/ማዋረድ በአካል የመገናኘትና የመግባባት ስልጠና እና ፕሮግራሚንግ መፍጠር።
- ዛቻ፣ ማስፈራራት፣ ማሸማቀቅ፣ እና ጾታዊ-ወሲባዊ ጥቃትን ስለመከላከል እና ምላሽ ስለመስጠት አሰልጣኞችን እና ስፖንሰሮችን ለማሠልጠን እንዲችሉ ለአትሌቲክስ ዳይሬክተሮች እና ለአስተዳዳሪዎች በአካል የመገናኘትና የመግባባት ስልጠና እና ፕሮግራሚንግ መፍጠር።
- ለአስተዳዳሪዎች፣ ለአትሌቲክስ ዳይሬክተሮች፣ ለአሰልጣኞች እና ለስፖንሰሮች ስልጠና በሚሰጥበት ወቅት የአነጋገር/የቃላት ለዛ "tone at the top" እና ዛቻ፣ ማስፈራራት፣ ማሸማቀቅ፣ እና ጾታዊ-ወሲባዊ ጥቃትን ስለመከላከል ተማሪዎችን የማሳተፍ አስፈላጊነት ላይ ትኩረት መስጠት።

## III. ጠንካራ/ጤናማ የቁጥጥር ስልቶችን ተግባራዊ ማድረግ

### የፌብሩወሪ 2019 የቁጥጥር-እቅድ መስፈርት

### ግኝቶች

- ስለ ቁጥጥር-ፕላን መስፈርት አንድ አይነት ያልሆነ/የተደባለቀ ምልከታዎች ታይተዋል።
- የቁጥጥር እቅዶቹ በጥራት ይለያያሉ።
- በጣም ጥልቀት ያላቸው እና ለመተግበር የሚያስችሉ ፕላኖች/እቅዶች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሁሉ ጋር በመተባበር የተዘጋጁት ናቸው።
- የአትሌቲክስ ዳይሬክተሮች እና አሠልጣኞች ስላዘጋጁቸው የቁጥጥር ፕላኖች/እቅዶች ከአስተዳዳሪዎች እና ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ዋና ጽ/ቤት ግብረመልስ ጠይቀዋል።

### አስተያየቶች/ሪኮመንዴሽንስ

- ተከታታይነት ያለው እና የማያቋርጥ ቁጥጥር በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ላይ ማካሄድ የሚቻል አለመሆኑን እና አስፈላጊም እንዳልሆነ በግልፅ መነጋገር ያስፈልጋል።
- ለቁጥጥር እቅዱ ጠቃሚ የሚሆኑ ምርጥ ተሞክሮዎችን መሠረት ያደረገ ሊተገበር የሚችል መመሪያ መስጠት።
- አስተዳዳሪዎች፣ የህንፃ አገልግሎት የሚሰጡ፣ የፀጥታ/የጥበቃ ሠራተኞች፣ እና ሌሎችም የቁጥጥር ፕላን/እቅድ በሚያዘጋጁበት ወቅት በትብብር እንዲያደርጉ ማበረታታት።
- ትምህርት ቤቶች የሚያዘጋጁቸውን የሱፐርቪዥን እቅዶች በትክክል ሥራ ላይ ለማዋል እንዲችሉ ጥገናዎችን እና የሚያስፈልጓቸውን ሪሶርሶች መስጠት።
- አሁን በሥራ ላይ ያለውን በተማከለ የአስተዳደር የሚሰጡ የአትሌቲክስ እና ከመደበኛ ትምህርት በተጨማሪ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ድጋፍ መገምገም/ክለሳ ማድረግ።

## ተጨማሪ የቁጥጥር/ሱፐርቪዥን ተግዳሮቶች

### ግኝቶች

- በተለያየ አይነት የሚተገበሩ መርሃግብሮች በትምህርት ቀን መጨረሻ እና ተግባራዊ በሚደረግበት መጀመሪያ ላይ "የቁጥጥር-ክፍተት" ይኖራቸዋል።

- የትምህርት ቤት አሠልጣኞችን የበለጠ መጠቀም የሱፐርቪዥን/የቁጥጥር ችግሮችን ለማሻሻል/ለማቃለል ይረዳል።
- በጠቅላላ ዲስትሪክቱ ውስጥ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ተጨማሪ የጥበቃ ሠራተኞች እንደሚያስፈልጓቸው ተመሣሣይ ሪፖርት አቅርበዋል።
- የመቆጣጠር ኃላፊነቶች አብዛኛውን ጊዜ የሚወድቁት በህንፃ አገልግሎት ሠራተኞች ላይ ነው።
- በርካታ ተማሪዎች ከልምምድ በኋላ እና ሌሎች ከትምህርት ሠዓት በኋላ ያሉ እንቅስቃሴዎቹ እንዳበቁ በፍጥነት ትምህርት ቤት የመልቀቅ ችግር አለባቸው።
- ሱፐርቪሽን/ቁጥጥር ይልቁንም የካምፓስ ፋሲሊቲዎችን ለ Interagency Coordinating Board ("ICB") ሁነቶች በመጠቀም ይበልጥ ይወሳሰባል።

## ሪኮመንዴሽንስ/አስተያየቶች

- ከትምህርት ሠዓት በኋላ ተጨማሪ የጥበቃ ሠራተኞችን መመደብ ያስፈልጋል።
- የመጨረሻው ደወል ከተደወለ በኋላ ልምምድ እስከሚጀመርበት ጊዜ ድረስ ባለው ክፍተት ተማሪዎች ለእይታ/ለቁጥጥር አመቺ በሚሆን ስፍራ ላይ እንዲቆዩ ማድረግ።
- መምህራን ከመደበኛ ከሪኩለም ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ላይ ስፖንሰር የማድረግ እና የሚወስዷቸውን ኃላፊነቶች መገምገም።
- የአክቲቪቲ አውቶቡሶችን የጊዜ ሠሌዳ ማራዘም ወይም ማዘዋወር።
- አሁን በሥራ ላይ ያሉት መደቦች እና የሥራ መግለጫዎች ከመደበኛ የትምህርት ሠዓት በኋላ ያለውን የሱፐርቪዥን ክፍተት ለማሻሻል ይጠቅም እንደሆነ ግንዛቤ መወሰድ አለበት።
- የህንፃ አገልግሎት ላይ የሚሠሩ ሠራተኞች ከመደበኛ የትምህርት ሠዓት በኋላ ባለው ጊዜ ለሚካሄደው የሱፐርቪዥን ሥራ አንድ አካል የመሆን ሚና እንዳላቸው በስልጠና የተደገፈ ማረጋገጫ መስጠት ያስፈልጋል።
- ሱፐርቪዥን እና ደህንነትን በሚመለከት ትምህርት ቤቶች የአትሌቲክስ ዳይረክተሮችን እና አስተዳዳሪዎችን በአንድ ላይ እንዲወያዩ ማድረግ እንዳለባቸው ማበረታታት።
- በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ላይ አሁን በሥራ ላይ ያለው የማህበረሰብ ተጠቃሚነት ፖሊሲ የተማሪዎችን ደህንነት እና የሱፐርቪዥን ተግባርን የሚያካትት መሆኑን ለማረጋገጥ ከ ICB ጋር በጋራ መሥራት።
- ትምህርት ቤቶች በመካሄድ ላይ ያሉ ተማሪዎችን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ከአሠልጣኞች እና ከስፖንሰሮች ጋር በቀጥታ ለመገናኘት የሚችሉበትን ስልት እንዲያዳብሩ መርዳት።
- ክስተቶች ሲፈጠሩ፣ በፍጥነት ስለ ሁኔታው ሪፖርት የሚሰጥ ሰው እንዲኖር ማበረታታት።
- ለትምህርት ቦርድ እና ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አትሌቲክስ እና ከመደበኛ ከሪኩለም ተጨማሪ ፕሮግራሞች ዓመታዊ ገለጻ መሰጠት እንዳለበት ግምት ውስጥ ማስገባት።

### ስለተፈጠሩ ክስተቶች ወቅታዊ የሆነ ሪፖርት መቅረቡን እና ተገቢ ምላሽ መሰጠቱን ማረጋገጥ

### ግኝቶች

- የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የግዴታ ሪፖርት መደረግ ያለባቸው መስፈርቶችን እና ቅደምተከተሎችን በሚመለከት ጠንካራ/ጤናማ ዲስትሪክት አቀፍ ደንቦችና መመሪያዎች አሉት።
- አስተዳዳሪዎች እና የአትሌቲክስ ዳይሬክተሮች ሪፖርት ስለማድረግ ያለባቸውን ግዴታ ያውቃሉ።
- አሠልጣኞች እና ስፖንሰሮችም ሪፖርት የማድረግ ኃላፊነት እንዳለባቸው መሠረታዊ የሆነ ሊያሠራቸው የሚችል ግንዛቤ አላቸው።
- አብዛኛዎቹ አሠልጣኞች እና ስፖንሰሮች ቅጽ 230-35 የመሙላት ኃላፊነት የአስተዳዳሪዎች ኃላፊነት እንደሆነ አድርገው ያስባሉ።
- ተማሪዎች በበኩላቸው ይፋዊ ያልሆነ በመለስተኛ ሁኔታ ሪፖርት እንዲደረግ ይመርጣሉ።
- ተማሪዎች በይፋ ሪፖርት እንዲደረግ በማይፈልጉበት ጊዜ የሥራ ባልደረቦች ወይም መምህራን ምን አይነት ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው በ Regulation JHF-RA ላይ የተገለጸ ነገር የለም።
- ከመደበኛ የትምህርት ሠዓት በኋላ ስለሚፈጠሩ ክስተቶች ሪፖርት አቀራረብ እና ሥነስርዓት በደምብ የዳበረ ነገር ስለሌለ አስቸኳይ የሆነ ምላሽ ያስፈልገዋል።

## ሪኮመንዴሽንስ/አስተያየቶች

- የትምህርት ቤት ቀን ካበቃ በኋላ ስለሚፈጠሩት ክስተቶች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የሪፖርት አቀራረብ ስነ-ስርዓት እንዲያዳብሩ ትምህርት ቤቶችን ማበረታታት።
- ተማሪ ሪፖርት እንዲደረግ ፍላጎት እንደሌለው/እንደሌላት ቢገልጹም እንኳ አስተዳዳሪዎች እና የሥራ ባልደረቦች በሙሉ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ እንዳለባቸው ማወቃቸውን ማረጋገጥ።
- ቅጽ 230-35 ሚናው ምን እንደሆነ በግልጽ ማስቀመጥ፡፤
- ከተማሪዎች መረጃዎችን ቀደም ብሎ መሰብሰብ።
- ማሻሻል የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ለመለየት የተከሰቱ ሁኔታዎችን ዳታ/መረጃ በየጊዜው መገምገም።